

# የትግራይ ሱሪ ከአሉላ ጋር አብሮ ተቀበረ
## (በወርሃ የካቲት ትግራይ ጉድ ወለደች)



ከበላይ ገሰሰ

የዮሐንስ የራስ አሉላ ሀገር
አንገቱ የሰጠ ለወገኑ ክብር
በጀግኖች አጥንት የታጠረ ዳር ድንበር
በደም የተፃፈ የታሪክ ማሕደር።
ዛሬ በባዕድ ተደፈረ
ፍትሕ በሐሶት ተቀየረ
የወላጅ አደራ ተሰበረ
ወገን ታጣ የጠነከረ
የትግራይ ሱሪ ከአሉላ ጋር ተቀበረ።



የዮሐንስ አገር የራስ አሉላ
ዛሬ ትግራይ ጉግ ማንጉግ አብቅላ
የሰላም ፀር እሾኽ አሜኬላ
እናቱን የሚሸጥ የባዕድ ደላላ
የሳህል ምንደኛ የውጭ ዲቃላ
በአውራጃ በዘር ተከፋፍላ
ወገን አጣች የሚሆን ከለላ
የሞተላት ቀርቶ የገደላት በላ።



የዮሐንስ መሬት የጀግኖች ምድር
የአባቶች እትብት የአሉላ መቃብር
አንበሳ ተኝቶ ዝንጀሮ ሲጨፍር
ህዝብ ሲንገላታ ነፃነት ሲቸረቸር
ጎሮሮ ተዘግቶ መግቢያ መውጫ በር
እናት ሀገራችን ሽባ ሆና ስትቀር።

እውነት የካቲት የትግራይ ልደት?
ወይስ የሀገር ገመና የክሕደት
የጨለማ ቀን የደም ሰንበት
የውርደት በዓል የወገን ባርነት
ጥቁር ታሪክ የትውልድ ሀፍረት።



ዓይደር
የህፃናት መልግብ
የዕልቂት መንደር

ሽፍታ በህዝብ ደም ሲነግድ
በሀገር ላይ ከሃዲ ሲቀልድ
ዜጋ ሲታሰር ሲሰቃይ ሲሰደድ
ቤቱ ሲቃጠል በቦምብ ሲነድ
ወገን ታጣ ፈጥኖ ደራሽ ዘመድ
ፍርሃት ነገሰ ተኰላሸ ትውልድ
የእሳት ልጅ ተወለደ አመድ።



እነ አቶ ሽብሩ እነ አቦዬ አይነጋ
የባዕድ ወኪል የከሃዲ መንጋ
ክብራችን ሲሸጡ ለርካሽ ዋጋ
ሰላም ደፍርሶ ሀገር ሲናጋ
ዓይናችን እያየ በራችን ሲዘጋ
በቁም እንቅልፍ ስንዘናጋ
ጆሯችን ቆርጠው ሲሰጡን ስጋ።

ታዲያ!! ይኼው ነው ልማቱ ድግሱ?
ከደደቢት ከጥዋቱ ከጥንሱሱ
የካቲት አሃዱ ብለው ሲነሱ
በማር ጠቅልለው መርዝ ሲያጎርሱ
ባህላችን በርዘው ታሪክ ሲያራክሱ
ሉዓላዊ ክብር ሀገር ሲያፈርሱ
የቀበሮ ቡድን የበግ ቆዳ የለብሱ
ምስለ ሻዕቢያ ደመኞች ነገሱ።

ለጠላት መንበርከክ ለባዕዳን ዓለም
ታሪክን መለወጥ በሰው ስራሽ ቀለም
በፍፁም!! የትግራይ ባህል አይደለም።

አባ ታጠቅ መይሳው ካሳ
የሐንስ መተማ የማይረሳ
የታሪክ አሻራ የድል አንበሳ
ምን ይል ነበር? ዛሬ ከመቃብር ቢነሳ?

የጀግኖች አገር የራስ አሉላ
ዛሬ ትግራይ ጉግ ማንጉግ አብቅላ
የሰላም ፀር እሾኽ አሜኬላ
እናቱን የሚሸጥ የባዕድ ደላላ
የሳህል ምንደኛ የውጭ ዲቃላ
በአውራጃ በዘር ተከፋፍላ
ወገን አጣች የሚሆን ከለላ
የሞተላት ቀርቶ የገደላት በላ።

ጥቂት ተጋሩ የባዕዳን ባንዳ
ለአኩይ አላማ ለሕቡእ አጀንዳ
ሳህል ተጠንስሶ ደደቢት ተወልዳ
ዛሬ ትግራይ ተሸከመች መከራና ዕዳ
መቋጫ የሌለው የትውልድ ፍዳ።

በሀይል ሲገዛ ዘራፊ ግፈኛ
ማን ይሁን ከሳሽ ማን ይሁን ዳኛ
በገዛ ሀገሩ ሆኖ ጥግኛ
በገዛ መሬቱ ሆኖ ጢሰኛ
በገዛ ሙብቱ ሆኖ ምፅዋተኛ
የበይ ተመልካች ሆኖ ተስፈኛ
ወኔው ተሰልቦ ሲሆን ሞርኰኛ
ውሽማ ይገባል ባለቤት ሲተኛ።

ሀብት የሚዘርፍ እየቦረቦረ
ለውጭ የሚሸጥ ባህር እያሻገረ
ያባቶች አደራ ቃል ኪዳን የሰበረ
የባዕድ አሽከር ለጥቅም ያደረ
የካቲት ጉድ ወለደች ቂመኛ ካድረ
የትግራይ ሱሪ ከአሉላ ጋር ተቀበረ።

ወኔ የሌላው ሆድ አደር
ሕግ የማይገዛው ስነ ምግባር
ታሪክ አጉዳፊ የሰላም ፀር
ከፋፋይ በኃይማኖት በዘር
ባህል የሌለው የወገን ፍቅር
ጨካኝ አውሬ የመጣ ከዱር።

በጠላት ስር ወድቃ እናት ስትደማ
ወገን ሲሰቃይ ታጉሮ በመጨላማ
ወላድ መኻን ሆነች እማማ እማማ
ልጄ ልጄ እያለች ድምፅዋ ስታሰማ።

የቀውጥ ቀን ፈጥኖ ደራሽ
ወገን ታጣ የሚሰጥ ምላሽ
ልጅ ጠፋ ጀግንነት ወራሽ
ለሆዱ አደረ ለፍርፋሪ ቁራሽ።

ይገርማል የናት ሆድ ዥንጉርጉር
አንዱ ለሀገር ሌላው ለወንበር
አንዱ ለህዝቡ ሌላው ለገንዘቡ
አንዱ ለሃቅ ሌላው ለስርቅ
አንዱ ለእውነት ሌላው ለውሸት
አንዱ እየለማ ሌላው እየተጠማ፡፡

ሽፍታ በህዝብ ደም ሲነግድ
በሀገር ላይ ከሃዲ ሲቀልድ
ዜጋ ሲታሰር ሲሰቃይ ሲሰደድ
ቤቱ ሲቃጠል በቦምብ ሲነድ
ወገን ታጣ ፈጥኖ ደራሽ ዘመድ
ፍርሃት ነገሰ ተኰላሽ ትውልድ
የእሳት ልጅ ተወለደ አመድ።

በጠላት ስር ወድቃ እናት ስትደማ
ወገን ሲሰቃይ ታጉሮ በመጨላማ
ወላድ መኻን ሆነች እማማ እማማ
ልጄ ልጄ እያለች ድምፅዋ ስታሰማ።

አንተ!! የለውጥ አንቀሳቃሽ ተማሪ መምህሩ
ወጣት ሽማግሌ ገበሬ ላባደሩ
ሙስሊም ክርስቲያን መስጊዱ አድባሩ
ሙዚቀኛ ደራሲ ኪነት መዘምሩ
ሰዓሊ ጋዜጠኛ መሳሪያው ብዕሩ
ሀገር ወዳድ ሁሉ ዜጎች በድምሩ
ለወገን ጥብቅና ካልጮኹ ካልተነጋገሩ
ምንድን ነው ትርጉሙ በዚህ ዓለም መኖሩ።

አንተ!! የሀገር ልጅ ስማ ባለሙያ
መለዮ ለባሹ ያገር መከላኪያ
እንደ ሌላው ቦታ እንደ ቱኒዝያ
ፍትሕ እንዲነግስ በእናት ኢትዮጵያ
ሀገር ሲኖር ነው ከሁሉም ቅድሚያ
ህዝባዊነትህ ነው ያንተው መለኪያ
ወገንን ለማዳን ለመሆን መኩሪያ
የህዝብ ሀብት ነው የያዝከው መሳሪያ።

ሁሉም ካልነቃ ካልተባበረ
ከእንቅልፉ ካልባነነ ካልጠነከረ
የሰደድ በሽታ ፍርሃት ካልሰበረ

ሌላ የለም አማራጭ ቁምነገር
እርዳታ የሚሰጥ ነፃነት የሚቸር
መፍትሔው እኛ ነን ስንተባበር
ጠላት ሳይቀድመን በቁም ሳንቀበር
ብለን እንነሳ ቀልድ የለም በሀገር።

ከበላይ ገሰሰ